PANORAMA # XXXV

# የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓም

## ትቢያ በራሱ ላይ እየነሰነሰ የሚኖር አገዛዝ

ተፈጥሮን ተመክሮ አያድነውም እንዲሉ፥ የጎጠኛው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ሥርዓት፥ ተጠጋግኖ፥ ተለሰኖ፤ ተውሸልሽሎና ተደርቶ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ ይመስል፥ ደጋፊዎቹ ተስፋ ባለመቁረጥ ቅብዓ-ሚሮን ሊቀባቡት እየሞከሩ ይገኛሉ:: ተስፋ ያልቆረጡት ተከታዮቹና እበላ ባዮች አገልጋዮቹ፥ ሥርዓቱን ለመጠጋገን ቢሞክሩም፥ መለስና ግብረ-አበሮቹ ግን አሁንም በራሳቸው ላይ ትቢያ እየነሰነሱ አስቸግረዋቸዋል:: በኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውንም ሕዝባዊ ትግል ለማሰናከልና የሕዝቡንም ስትራተጂያዊ አቅጣጫና ሀገር የማዳን ትኩረት ለማሳት የሚደረገውን ከንቱ መፍጨርጨር ስንመለከት፥ ታሪክ እራሷን በተለያየ መልክና ወቅት ትደግማለች የሚለውን አባባል ለመቀበል እንገደዳለን:: ሁል ጊዜም ቢሆን አንድ አምባገነን ሥርዓት እየበሰበሰ፥ እየተናደና እየተፍረከረከ በሚሄድበት ወቅት፥ የዚያ ሥርዓት አቀንቃኞችና ተጠቃሚዎች፥ ሥርዓቱ ከፃዕረ-ሞት እንዲተርፍ ይሯሯጣሉ:: ይህ ክስተት በአፄውም ሆነ በደርግ የመጨረሻ ስዓታት የታየ ሀቅ ነበር:: የፊውዳሉን ሥርዓት ለማዳን የአስቸኳይ አምቡላንስ ለመጥራት ሲደረግ የነበረውን መቅበዝበዝ ለማስታወስ አይከብድም:: ደርግ በሚፍረከረክበትም ጊዜ እንደዚሁ፥ የመጨረሻዋን 11ኛ ስዓት እንጠቀም ያሉ ሰዎች እንደነበሩ የቅርብ ትዝታ ነው:: መንግሥቱ ኃይለማርያም ጥሏቸው ሲሸሽ ግን፥ " ዋይ ዋይ! እያለ ሄደ፥ ዋይ ዋይ!" እያሉ ሙሾ ደርድረውለታል:: ሀገሪቱን ግን ለወያኔ አሳልፈው ሰጧት እንጅ፥ መፍትሄ አላስገኙላትም:: የሚገርመው ደግሞ ትላንት በመንግሥቱ ግብዐ-ተመሬት ላይ ሙሾ ሲያቀነቅኑ የነበሩ ግለሰቦች፥ ዛሬ ተመልሰው ወያኔ ጠላት አይደለም እያሉ ራሳቸውን ለታሪክ ትዝብትና ውርደት አሳልፈው መስጠታቸው ነው::

አሁንም ካለፈው የሀገሪቱ ታሪክም ሆነ ከተመክሮ ያልተማሩ ክፍሎች፥ ተመሳሳይ ድርጊት እየፈፀሙ ይገኛሉ:: መከራ ያልመከረውና ያላስተማረው ሰው ምን እንደሚያስተምረው ግን መረዳት ያስቸግራል:: ይህች ተአምረኛ ሀገር ደግሞ ሁል ጊዜ በታሪክ ምፀትና በዘመን ፅንቆቅልሽ አዙሪት እየገባች ትሽከረከራለች:: የሕዝቡም መከራና ፍዳም በዚሁ በማያቋርጥ መንኮራኩር ውስጥ ሆኖ እንምቧለሌ ይዞራል:: ከዚህ ጭቆና ቀንበር ለመውጣት አዲስ ራዕይና አቅጣጫ እንደመፈለግ፥ አሁንም ሕዝቡን፥ ያው በአሮጌ የመከራና የጭቆና ድሪቶ ተተብትቦ እንዲገዛ ይደረጋል:: ዙሪያው ገደል የሆነበት ሕዝብም በበኩሉ፥
" ተሸካሚ ሆንኩኝ መከራና ጣጣ፤ ቀንበሬን የሚያወርድ ማን አርበኛ ይምጣ?" እያለ የመከራ ህይወቱን ይገፋል:: ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሚሆን የፖለ

ቲካ፥ የምጣኔ ኃብትና የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓት እንደመትለም ፈንታ፥ የዘረኞችን አገዛዝ ለመጠጋገን እየተሞከረ ነው። አሁንም ያው እንደተለመደው የሥርዓት ለውጥ ከማምጣት ይልቅ፥ በአረጀ- በአፈጀ የዘረኞች ፈረስ ለመወዝወዝ እየተጣረ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ ገፅታዋ ስትታይ በዓለም የመጨረሻዋ ደሃ ነች እየተባለ ዘወትር ሲነገረን እያየን እየሰማን፥ ሊቆረቁረን ፥ሊያንገበግበን፥ ሊያሳፍረንና ሊቆጨን ሲያንስ ነው። ሌላው ቀርቶ በሃያኛ አንደኛው ምዕተ ዓመት፥ በዓለም ውስጥ በጎሳ ላይ በተመሠረተ ሥርዓት የምትተዳደር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን እንኳን ተረድተን፥ ይህንን ጎሰኛና አሳፋሪ ቡድን ለመለወጥ መነሳት አለብን። ያማ ባይሆን ኖሮ፥ መለስና ግብረአበር ጎጠኞች ለ17 ዓመታት፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ባልተጫወቱባት ነበር፥ ባላጠፏትም ነበር። መለስ ዜናዊ፥ "ጀግና የሆነ መጥቶ ይሞክረኝ" እያለ ሲደነፋ፥ የኃፍረት አንገት መድፋት ብቻ ሳይሆን፥ በፍርኃትም ማቅ ተሸፋፍነን እንገኛለን። በመሆኑም መለስና ግብረ-አበሮቹ የልብ ልብ ተሰምቷቸው፥ ያሻቸውንም እያደረጉ ይገኛሉ። የራሳችንን ሀገር ሌላ መጥቶ ነፃ የሚያወጣልን እየመሰለን፥ "አሜሪካ ይህን አድርጎ፥ አውሮፓውያን ይህን ሠርተው" እያልን የመፅናኛ ምክንያት በመፈለግ ጊዜያችንን ማጥፋት አለብን። አቅጣጫችንንም እንበታትነዋለን። ቀፎው ሲነካበት እንደሚቀሰቀስ ንብ ቆርጠን ካልተነሳን፥ ማንም መጥቶ ከመከራችን፥ ከውርደታችንና፥ ከኃፍረታችን ነፃ ሊያወጣን አይችልም። ቀደም ሲል በነበረው ታሪካችን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነቱን ሊገፍፈው የሚመጣውን ሁሉ አሳፍሮ ከመስደድ በቀር፥ ሕዝባችን በዋና ደረጃ የማንንም ርዳታና ድጋፍ አስፈልጎት አያውቅም ነበር ። "ሀገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል" ሆኖብን ነው መሰል፥ ዛሬ ወያኔን የመሰለ የውስጥ ጃርት በቅሎበት ለውጭ ጠላትም ጥቃት ተዳርጓል።

ከቀን ወደ ቀን የራሱን መቃብር እየቆፈረና የመቃብሩንም አፈር በራሱ ላይ እየነሰነሰ ያለውን ሥርዓት ነፍስ ለመዝራት ታስቦ፥ የወያኔ ካድሬዎች በአውሮፓና በአሜሪካ ስደተኛውን ለመደለልና ለመከፋፈል ሙከራቸውን በሰፊው ተያይዘውታል። በአሁኑ ወቅት፥የጥፋት መልዕክተኞቹ፥ በአሜሪካን ሀገር በሚገኙ ጥቂት ከተሞች ማለትም፥ በዋሽንግተን ዲሲ፥ በሲያትል፥ በዴንቨር፥ በሳን ሆዜ፥ በዳላስ፥በጠሯቸው ስብሰባዎች፥ በሕዝቡ ዘንድ እየተዋረዱና እየተሸማቀቁ እንደሆኑ ተረጋግጧል። የዚህ ያልተሳካ ስብሰባና ተልዕኮ ዓይነተኛ አጀንዳም፥ "ሀገር ብትገቡ፥ መሬትና ንብረት ትታደላላችሁ፥ ሹመት ሽልማትም ይለገስላችኋል" የሚል እንደነበረ ስብሰባቸውን እየረገጡ ከውጡት ታዛቢዎች ለመረዳት ተችሏል። ይህንን ተልዕኮ የሚመሩት የወገኖቻቸውን የኀገለ ደም ረግጠው የመጡ ለሆዳቸው ብቻ የሚኖሩ የየአካባቢው ተወላጆችና የወያኔ ኮር አባላት እንደሆኑ ል። በሌላ በኩል ደግሞ የወያኔ ዳስ ሰሪና አሳለፊነትን ለማረጋገጥ፥ ይህንን ያልተሳካ ጉዞ የሚያቀነበባብሩት በየቦታው ያሉ የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ ተደርሶበታል። "ዘር ከልጓም ይስባል" ስለሆነ ይህ አያስደንቅም። ከዚህም በላይ፥ "በልትን እንሙት እንጅ፥ ኢትዮጵያ እንደሆነች የሚያልፍላት ሀገር አልሆነችም" ብለው ተስፋ የቆረጡና ከትግሉ መድረክ የተፈናቀሉ ክፍሎች

በድብቅ እንደተገናቸው ታውቋል፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ እየከዱ ከሀገር ጠላት ጋር የሚወግኑ ሰዎች በዘመናት ፍርርቅ ሲከሰቱ እንደነበር የታወቀ ነው የሚሉ ተመልካቾች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በወ.ጨ. ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ሊኖራቸው የሚችለውን ሚናና የሚያስከትልበትንም አደጋ ከማንም በበለጠ የተረዳው እራሱ ወያኔ በመሆኑ፥ በውጭ ሀገር ያለውን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ተቃውሞ ለማደናቀፍ መሞከሩ ከወያኔ የማይጠበቅ አልነበረም፡፡ ሊያስገርም የሚችለው ይኸንን ሳያደርግ ቢቀር ነበር፡፡ መለስና ግብረ-አበሮቹ፥ ይህንን የውጭ ተቃውሞ ቢቻል ለማጥፋት ካልሆነ ደግሞ ለመከፋፈልና ለማድከም አምሳ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መድቦ እንደሚንቀሳቀስ ማነኛው በውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሚገባ ያውቀዋል፡፡ የወያኔ ሙከራ በቀላሉ ባይገመትም፥ የኋላ ኋላ ግን እንደሚከሽፍ ከወዲሁ ተረጋግጧል፡፡ ምክንያቱም፥የመከነ ኃሳብና ፀረ-ሕዝብ ሴራ ሁሉ ተጨናግፎ እንደሚቀር የተፈጥሮ ህግ በመሆኑ ነው፡፡

ከውስጥ አዋቂዎች ከተገኘው መረጃ ለማወቅ እንደተቻለው፥ የወያኔ ቅጥረኛ ነገር ሰሪዎች ፥ወያኔ የኢትዮጵያን የምዕራብ ግዛት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ ምክንያት ከተቋቋመው የወሰን ( ቦርደር) ኮሚቴ ውስጥ ሰርስረው በመግባት የሕዝቡን መነሳሳትና ተቃውሞ ለማኮላሸት ያደረጉት ሙከራ እንደከሸፈባቸውና ሰላዮቹም እንደተጋለጡ ተረጋግጧል፡፡ ሌሎች የወያኔ አጫፋሪዎችና ፀረ አንድነት ክፍሎችም በበኩላቸው፥ በዋሽንግተን አካባቢ በማንዣበብ ላይ እንደሚገኙ የዓይን ምስክሮችና ተከታታዮች አረጋግጠዋል፡፡ ከተሳካላቸውም፥ ያው እንደተለመደው፥ በሕብረተሰቡ ዘንድ ብዥታና አሉባልታ በመንዛት የአንድነት ኃይሉን ለመከፋፈል መጣራቸው አይቀርም፡፡ ዛሬ ወያኔ በሞት-ሽረት ላይ በሚገኝበት በዚህ ወሳኝና ቀውጢ ሰዓት መለስና ግብረ-አበሮቹ በውጨ ነዋሪ ኢትዮጵያዊው ያለውን ተቃውሞ በሆነው መንገድና ዘዴ ተጠቅመዉ ለማኮላሸት እንደሚጥሩ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ እንደተረዳነው፥ ኅብረተሰቡ፥ ይህንን የወያኔን ሴራ ለማክሸፍ አስፈላጊውን ሁሉ እያደረገ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በአለፈው ጊዚያትም በተመሳሳይ መንገድ የወያኔን ሴራ እንዳከሸፈበት የሚታወስን ነው፡፡ ያም ሆኖ፥ የወያኔ የመረጃ ሰዎች ሥራቸውን አይሰሩም ብሎ የሚያስብ ማንም የለ፡፡ ከአዘናጊዎቹና ከትጥቅ አስፈችዎች በቀር፡፡ ወያኔን ጠላት ነው አትበሉ የሚሉ በሦስት ተፈራራቂ ሥርዓቶች ካባቸውን እንደ የሁኔታው እየለዋወጡ የሚኖሩ አሳፋሪዎችም የሚያደርጉትን ትጥቅ አስፈች ዘመቻ በየትም ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እየታዘባቸውና እያጋለጣቸው እንደ ሆነ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል፡፡

ይህ ሁሉ ትንቅንቅና መፍጨርጨር የሚደረገው፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ በመንታ መንገድ ላይ በወደቀችበት ወቅት ነው፡፡ ሕዝቧም በከባድ ፈተና ላይ በአለበት ስዓት ነው፡፡ በአንድ በኩል የፀረ አንድነት ኃይላት እርሿቸውን አሟጥጠው በሞትና በሽረት መካከል ባለ ፃዕረ-ሞት ላይ ሆነው “ የአልሞት ባይ ተጋደይ” መፍጨርጨር ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ደግሞ

የአንድነት ኃይሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሞት-ሽረት ትግል ለማድረግ ራዕዩን አጥርቶ ኃይሉን አጠናክሮ የትግል አጋሮቹን በአንድ ጎራ አሰልፎና አቀናጅቶ፥ ሀገሩን ከጥፋት የሚያድንበትን ትግል በማካሄድ ላይ የሚገኝበት ወቅት ነው:: በዚህ ወሳኝ ወቅት ያለው ምርጫ ሁለት ብቻ መሆኑን አጥብቀን እናምንበታለን:: ጎራውም ሁለት ብቻ ነው:: አንደኛው ወያኔን አጫፍሮ በመቆም የለየለት የሀገር ጠላትነቱን ማስመስከር ሲሆን፥ በሌላ ወገን ደግሞ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን በሚደረገው ብሔራዊ ትግል ለኢትዮጵያ አንድነት ከቆመው ኃይል ጎራ ተሰልፎ መቆም ነው:: በዚህ ወሳኝ ታሪካዊ ወቅት፥ መሀል ሰፋሪ ሊኮን አይቻልም:: ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የተለያዩ ሰዎች/ ክፍሎች፥ በተለያዩ ምክንያቶች ወሳኝ አቋም ሊወስዱ አልሆነላቸውም:: ከእንግዲህ ወዲህ ግን አይተነው ጊዜ ወደ አደላበት የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም:: ሀገራችን ከቀን ወደ ቀን ኅልውናዋ እየጠፋ በሚሄድበት ወቅት፥ ገለልተኛ ሆኖ መገኘት ትርፉ የታሪክና የትውልድ ተወቃሽ ሆኖ መቅረት ብቻ ነው:: በመሠረቱ፥ በሀገር ጉዳይ ገለልተኛ መሆን ይቻልም:: እበላ ባይነት ካልሆነ በስተቀር! ወያኔ መቃብሩን እየቆፈረና አፈሩንም በአናቱ ላይ እየነሰነሰ ያለ ዘረኛ ቡድን ስለሆነ፥ ወደ ከርሰ-መቃብሩ ወርውሮ ሀገርን ከማዳን የበለጠ ታላቅና ሀገራዊ ጥሪና ተልዕኮ አይኖርም:: ለኢትዮጵያ ህልውናና ለሕዝቧ አንድነት የቆመውን ኃይልና ክንድ፥ በሆነ በአልሆነ ምክንያት እያዳከሙ ለወያኔ ተጨባጭ ድጋፍ እየሰጡ ያሉ ክፍሎች ከአፍራሽ ተልዕኮአቸውም እንዲቆጠቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ፥ ዓለም ዓይኑን እንዲጨፍን አድርገው የምዕራባውያን ተገዥነታቸውን ሲያረጋግጡ፥ አዳዲስ ከሀዲዎች ለዚሁ ቧልት አጃቢ ሆኖ መገኘት ሕዝባዊነት ሳይሆን፥ ፀረ ሕዝብነት መሆኑም በግልፅ ሊነገራቸው ይገባዋል:: ሕዝባችን ነጋ ጠባ የሚመኘውና የሚፈልገው የነፃነቱንና የመብቱ ባለቤትነቱን እንጂ፥ እነ እገሌ የተወሰነ ቡድን መሪዎች የወያኔ ፓርላማ አባል ሆነው እንዲሰየሙ አይደለም:: የተለጣፊው መበራከት ለሕዝብ የሚያመጣው ፋይዳ ወይም ጥቅም ፈፅሞ የለም:: በመሆኑም፥ ቢረዝምም ቢያጥር፥ ቢለማም ቢከፋም፥ ሕዝብን የሀገሩና የመብቱ ባለቤት በሚያደርገው ትግል መፅናት እንጂ፥ ለራስ ጥቅምና ለወያኔ ሹመት መኳንበስ አሳፋሪ ተግባር ነው::

ግራም ነፈሰ ቀኝ፥ በዚህም ተባለ በዚያ፥ የኢሕአፓ አባላት አልፋና ኦሜጋቸው አንድ ብቻ ነው:: ይኸውም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በገቡት ቃል ኪዳን መሠረት በሀገራቸው የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብቱ ባለቤት እስኪሆን ድረስ በአይበገሬነት እየተሰው መታገል !!!!!

EthioLion.com